ግብዣ

በኖርዌይ የቋንቋ ስልጠና የትውውቅ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍን በተመለከተ ያለዎትን ሃሳብ ያሳውቁን!

ሰላም፣

በኖርዌይ ቋንቋ ስልጠና እና በኖርዌይ ውስጥ ባለው የትውውቅ ፕሮግራም ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በአገር አቀፍ የተጠቃሚ ዳሰሳ ጥናት ላይ እንዲሳተፍ ተጋብዟል።

በዚህ ስልጠና ውስጥ መሳተፍዎ ምን ዓይነት ተሞክሮ እንዳስገኘልዎ ጥቂት ጥያቄዎችን ለመመለስ ይህን አጋጣሚ እንደምትጠቀሙበት ተስፋ እናደርጋለን። የዳሰሳ ጥናቱ እርስዎ ሊመርጧቸው የሚችሏቸው ቋሚ የምላሽ አማራጮችን ይዟል።

የዳሰሳ ጥናቱን የሚያካሂዱት Norwegian Directorate of Integration and Diversity (IMDi፣ የኖርዌይ የውህደትና ብዝሃነት ዳይሬክቶሬት) እና Norwegian Directorate for Higher Education and Skills (የኖርዌይ የከፍተኛ ትምህርት እና ክህሎቶች ዳይሬክቶሬት) ናቸው።

እኛና የእርስዎ ከተማ አስተዳደር ለእርስዎና ሌሎች የትውውቅ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንድንችል፣ የእርስዎን ተሞክሮ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት እፈልጋለሁ።

መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ትክክለኛ መረጃ እናገኝ ዘንድ በሚሰጧቸው ምላሾች ላይ ግልጽና ታማኝ መሆን አለብዎት። ለምሳሌ፣ እርስዎ በተሳተፉበት ስልጠና እርካታ የተሰማዎት መሆን አለመሆኑን፣ በፕሮግራሙ ውስጥ መሳተፍ የሚያስደስትዎት ስለመሆኑና በፕሮግራሙ ውስጥ አሉታዊ የሆነ ነገር አለ ብለው የሚያስቡ ስለመሆንዎት ጥያቄ ይጠየቃሉ።

ተሳትፎ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፤ የተጠቃሚ የዳሰሳ ጥናቱን ለማጠናቀቅም በግምት ወደ 30 ደቂቃ ያህል ይወስዳል። የተጠቃሚ ዳሰሳ ጥናቱ ስም አልባ ነው። ምላሾችዎን ከእርስዎ ጋር ለማገናኘት አይቻልም፣ የከተማ አስተዳደሩም እርስዎ ምን ምላሕ እንደሰጡ ለማየት አይችልም።

የእርስዎ ከተማ አስተዳደር በተጠቃሚ የዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችልዎትን መግቢያ ይሰጥዎታል።

የዳሰሳ ጥናቱን የሚሞሉበትን ቋንቋ መምረጥ ይችላሉ። በገጹ በስተግርጌ ላይ ያሉትን የቋንቋ አዶ (አይከኖች) ይጠቀሙ። ሁሉም ጥያቄዎችና የምላሽ አማራጮች በጽሑፍና በድምፅ ቀርበዋል። የጥያቄ እና የምላሽ አማራጮችን ለማዳመጥ ከፈለጉ፣ የድምፅ አዶ (አይከን) ይጠቀሙ።

አጠቃላይ መጠይቁን በአንድ ክፍለ ጊዜ ማጠናቀቅ አለብዎት።

በተጠቃሚ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ ስለተሳተፉ እናመሰግናለን!

ከሰላምታ ጋር፣

Norwegian Directorate of Integration and Diversity (IMDi፣ የኖርዌይ የውህደትና ብዝሃነት ዳይሬክቶሬት) እና Norwegian Directorate for Higher Education and Skills (የኖርዌይ የከፍተኛ ትምህርት እና ክህሎቶች ዳይሬክቶሬት)